# ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ

## መግቢያ

የ2011 ዓ.ም ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ከግንቦት 21 –23 /2011 ዓ.ም **ለ 1,277,552**

የ10ኛና ከግንቦት 26 –30 /2011 ዓ.ም **ለ322,729** የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ 3,932 የፈተና ጣቢያዎች ይሰጣሉ፡፡ በመሆኑም በየደረጃው የሚገኙ ተፈታኞች ለፈተናው ተገቢውን ዝግጅት በማድረግና የፈተናን ህግና ደንብ አፈፃፀም በማክበር ለፈተናው መቅረብ ይገባቸዋል፡፡ የፈተናን መሠረታዊ ዓላማ ከሚያስቱ ጉዳዮች መካከል የፈተና ኩረጃ በዋነኛነት ይጠቀሳል፡፡

በተለያዩ ጊዚያት በተሰጡ ብሄራዊ ፈተናዎች ህገ ወጥ ተግባራትን በመፈጸም በማስረጃ የተረጋገጠባቸው በርካታ ተፈታኞች ውጤታቸው ተሰርዟል፡፡ የፈተና ኩረጃ ከመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጀምሮ እስከ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ድረስ የሚዘልቅ የትምህርት ስርዓቱ ነቀርሳ በመሆኑ ድርጊቱ ሊወገዝ ይገባል፡፡ የፈተና ኩረጃ አጸያፊ ተግባር መሆኑንና በተማሪው ላይ የሚያስከትለውን አፍራሽ ተጽእኖ ቤተሰብ፣ መምህራን፣ የት/ቤት አስተዳደርና የትምህርት ባለድርሻ አካላት ደጋግመው ለተማሪዎች በማስተማር የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡና በራሳቸው የመተማመን ባህርይ እንዲያጎለብቱ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተፈታኞች ፈተናውን በተረጋጋና ሰላማዊ በሆነ መልኩ ተፈትነው ተገቢውን ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚከበሩላቸው መብቶችና ሊያከብሩዋቸው የሚገቡ ግዴታዎች

## 1. የተፈታኞች መብት

- ማንኛውም ተፈታኝ በፈተና አሰጣጥ ወቅት መከበር ያለባቸውን ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች እንዲሁም የፈተና ጥያቄ ጥራዞችና የመልስ ወረቀቶችን አጠቃቀም አስመልክቶ በቂ ገለፃ የማግኘት መብት አለው፣
- ፈተናው በሚሰጥበት ጊዜ ትክክለኛ ያልሆነ የተቀደደ ወይም የተበላሸ የፈተና ጥያቄ ጥራዝ ወይም የመልስ ወረቀት ከገጠመው ወይም በፈተና ወቅት ከተበላሸበት ለፈታኙ በማሳወቅ ሊያስቀይር ይችላል፣
- ማየት ለተሳነው ተፈታኝ የፈተናውን ጥያቄዎች የሚያነብለት የሚሰጣቸውን መልሶች የሚያጠቁርለት ፈታኝ በግሉ ይመደብለታል፣
- የአካል ጉዳት ደርሶበት በራሱ እጅ መፃፍ የማይችል ተፈታኝ የሚያጠቁርለት ሰው በግሉ ይመደብለታል፣
- አንድ ተፈታኝ በፈተና ላይ እያለ የጤና መታወክ ችግር ቢገጥመው ለፈታኙ ችግሩን በመግለጽ እርዳታ ማግኘት ይችላል ሆኖም በማንኛው ምክንያት ለባከነ ጊዜ ተጨማሪ ሰዓት አይፈቀድም፣
- ማንኛውም ተፈታኝ የተሰጠውን ፈተና ተረጋግቶ፣ ሙሉ ችሎታውንና እውቀቱን ተጠቅሞ እንዳይሠራ የሚያውኩ ሁኔታዎች ከገጠሙት ስርአቱን ጠብቆ በመጠየቅ መፍትሄ እንዲሰጠው ማሳሰብ ይችላል፣
- ማንኛውም ተፈታኝ በሠራው ስራ ብቻ የፈተና እርማት እንደሚካሄድ በመረዳት የእንደገና ይታይልኝና ይመርመርልኝ ጥያቄ ተቀባይነት እንደማያገኝ አውቆ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

## 2 . የተፈታኞች ግዴታና ግዴታቸውን ባለማክበራቸው የሚወሰዱ የእርምት እርምጃዎች

- በፈተናው የመጀመሪያ ቀን የጠዋቱን ክፍለ ጊዜ ፈተና የሚፈተን ማንኛውም ተፈታኝ ፈተናው ከሚጀመርበት ጊዜ አንድ ሰዓት ቀደም ብሎ በፈተና ጣቢያው ቅጥር ግቢ መገኘትና አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ አለበት፡፡

በሌሎቹ የፈተና ቀናት ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ 30 ደቂቃ ቀደም ብሎ በፈተና ጣቢያ ቅጥር ግቢ መገኘት ይኖርበታል፡፡

- ማንኛውም ተፈታኝ ፈተናው ከተጀመረ ከ30 ደቂቃ በኋላ ወደ ፈተና ክፍል እንዲገባ አይፈቀድለትም፡፡ ፈተናው ተጀምሮ 45 ደቂቃ ካልሞላ ፈተናውን ሠርቶ ቢያጠናቅቅም እንዲወጣ አይፈቀድለትም፡፡ ይሁን እንጂ ፈተናው ከተጀመረ ከ45 ደቂቃ በኋላ ከፈተና አዳራሹ ለመውጣት ቢፈልግ በአግባቡ የፈታኙን ፈቃድ በመጠየቅ የጥያቄ ጥራዝና የመልሰ ወረቀቱን ለፈታኙ አስረክቦ በፀጥታ እንዲወጣ ይፈቀድለታል፡፡ በምንም ምክንያት ፈተናው እስኪጠናቀቅ ድረስ የፈተና ጥራዝ ይዞ መውጣት አይፈቀድም፡፡ ሆኖም ፈተናው ሊጠናቀቅ ከ15 ደቂቃ ያነሰ ጊዜ ሲቀረው የሚጨርስ ተፈታኝ የሁሉም ተፈታኞች የመልሰ ወረቀቶች እስኪሰበሰቡና ለፈተናው የተፈቀደው የጊዜ ገደብ አብቅቶ እስኪደወል ድረስ በቦታው በመቆየት የጥያቄ ወረቀቱን ይዞ መውጣት ይችላል፡፡
- አንድ ተፈታኝ የፈተና ጥያቄዎቹን መስራት ከመጀመሩ በፊት በፈተና መልስ ወረቀት ላይ የግል መለያ መረጃዎቹን በሙሉ ግልፅ በሆነ ሁኔታ በቅደም ተከተል መፃፍና በጥንቃቄ ማጥቆር አለበት፡፡
- እያንዳንዱ ፈተና በሚሰጥበት ጊዜ በሚቀርብለት የስም መቆጣጠሪያ ላይ በስሙ አንፃር የተመዘገበው የፈተና ቡክሌት ኮድ ከደረሰው ቡክሌት ኮድ ጋርና በመልስ ወረቀቱ ጫፍ ላይ በፈታኙ ከተፃፈው ቡክሌት ኮድ ጋር መመሳሰሉን አረጋግጦ  መፈረም አለበት፡፡ ማንኛውም ተፈታኝ ይህን ባለማድረጉ ለሚፈጠረው ችግር ኃላፊነቱ የራሱ ነው፡፡
- ማንኛውም ተፈታኝ የራሱን ችሎታና እውቀት ተጠቅሞ፤ የሚሠራባቸው የጥያቄና የመልስ ወረቀቶች ለሌሎች ተፈታኞች እይታ የተጋለጡ እንዳይሆኑ ሸፍኖ መስራት ይኖርበታል፡፡ ለሌሎች ተፈታኞች ድጋፍ መስጠትም ሆነ ከሌሎች መቀበል ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ ይህን የፈተና ደንብ በመተላለፍ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የፈተና ደንብ ጥሰቶች የፈፀመ ተፈታኝ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሎ ቀጣይ ፈተናዎችን እንዳይፈተን ይደረጋል፤ ህገ ወጥ ድርጊቱን ሲፈፅም ከመያዙ በፊት የተፈተናቸው የትምህርት ዓይነት  ውጤቶች በሙሉ ይሰረዛሉ፡፡

## 3 . ከላይ የተጠቀሰውን እርምጃ የሚያስወስዱ ከባድ የፈተና ደንብ መተላለፍ ጥፋቶች የምንላቸው የሚከተሉት ናቸው፡-

- በስሙና በተሰጠው የምዝገባ ቁጥር ሌላ ሰው ያስፈተነ ወይም በሌላ  ሰው ስምና ምዝገባ ቁጥር የተፈተነ፣
- በፈታኝ የሚሰጠውን ምክርና ተግሳፅ ባለመቀበል ሶስትና ከሶስት በላይ ፈተናዎች/የፈተና ክፍለ ጊዜዎች/ ተደጋጋሚ ጥፋቶች መፈፀሙ ሪፖርት የተደረገበት፣
- ከራሱ ፈተና ውጪ ለሌላ ተፈታኝ መልስ የሠራ፣
- ፈታኝን የሰደበ፣ በፈታኝ ላይ የዛተና ለመደብደብ የሞከረ፣
- የሌላን ተፈታኝ የፈተና ወረቀት(Booklet) ወይም የመልስ ወረቀት የቀማ ወይም ለመቀማት የሞከረ፣
- በፈተና ክፍል ውስጥ ሌላውን ተፈታኝ ፈተናውን ተረጋግቶ እንዳይሠራ ያወከና ማናቸውንም ዓይነት የኃይል ወይም የጉልበት ተግባር የፈፀመ፣

- በፈተና ወቅት የፈተና ጥያቄ ወረቀቱን ከፈተና ክፍል ውጭ እንዲወጣ ለማድረግ የሞከረ ወይም ያወጣ፣
- ሌሎች ተፈታኞችን በማዛደም የፈተና ክፍሉንም ሆነ የፈተና ጣቢያውን ሰላም በማወክ የፈተናውን ሂደት ለማስተጓጐል የሞከረ፣
- ለፈተና እንዲቀመጥ የሚያስችለውን የዓመቱን ትምህርት ያላጠናቀቀ፣
- በፈተና ክፍል ውስጥ ሞባይል ይዞ የተገኘ፣
- የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ተፈታኝ ሆኖ ለ10ኛ ክፍል ሲፈተን የተያዘ ተማሪ የተፈተናቸው ፈተናዎች ውጤቶች ከመሰረዛቸውም በላይ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናውንም እንዳይፈተን ይደረጋል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ከፍተኛ የፈተና ደንብ መተላለፍ ችግሮች አንፃር አቻ/እኩል ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች የፈተና ደንብ መተላለፍ ችግሮችን በፈፀመ ተፈታኝ ላይ ከላይ የተጠቀሱት የቅጣት እርማጃዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**ከዚህ በተጨማሪ፡- ቀላል የፈተና ደንብ መተላለፍ ችግሮች የምንላቸውን፡--**

- መኮራረጅ/ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ሆነው ፈተናውን በጋራ መሥራት፣
- ከውጭ ተሰርቶ የገባ መልስ ተጠቅሞ ፈተናው መስራት፣
- ሆን ብሎ የፈተና መልስ ማስቀዳት/መንገር ወይም በብጣሽ ወረቀት ጽፎ ለሌላ ተፈታኝ ማስተላለፍ ወይም የሠራበትን የፈተና ቡክሌት ለሌላ ሰው መስጠት፣
- የፈተና መልስ ከሌላ ተፈታኝ መቅዳት ወይም መልስ የተፃፈበት ብጣሽ ወረቀት ይዞ መገኘት ወይም ከሌላ ተፈታኝ መልስ የተሰራበት የፈተና ቡክሌት መቀበል፣
- ፈታኙ በመልስ ወረቀቱ አናት ላይ የፃፈውን የቡክሌት ኮድ መለወጥ፣
- አጫጭር ፎርሙላዎችንና ማስታወሻዎችን በብጥስጣሽ ወረቀቶች ወይም በሌላ መልክ ይዞ በፈተና አዳራሽ ውስጥ መገኘት፣
- በስሙና በምዝገባ ቁጥሩ በአንድ የትምህርት ዓይነት ፈተና ሁለት የመልስ ወረቀቶች ተሰርቶ መገኘት፣
- የፈተና መልስ መስጫ ወረቀቱን ሆነ ብሎ ማበላሸት ወይም መቅደድ፣
- አንድ ተፈታኝ ወደ ፈተና አዳራሽ ይዞ መግባት ከሚፈቀድለት የጽሕፈት መሣሪያ ማለትም እርሳስ፣ ላፒስ ማስመሪያና መቅረጫ ውጭ የተከለከሉ እንደ ካልኩሌተር፣ ሞባይል የመሳሰሉትን ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ይዞ ወደ ፈተና አዳራሽ መግባት፣
- በራሱ ፈቃድና በእምቢተኝነት ፈታኙ ከመደበው ቦታ /መቀመጫ/ ሌላ ቦታ ቀይሮ መገኘት፣
- በፈተና ጣቢያ ኃላፊው ወይም በረዳቱ በኩል የተደረገ የጊዜ ለውጥ ስለመኖሩ እስካልተገለፀ ድረስ አንድ ተፈታኝ የተፈቀደውን የጊዜ ገደብ ማክበር ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ ውጭ ለፈተና የተሰጠውን የጊዜ ገደብ አለማክበር፣
- ስካርቭ፣ ባርኔጣ/ቆብ፣ ሻሽና የመሣሰሉትን አድርጐ/ለብሶ ወደ ፈተና አዳራሽ መግባት በፍፁም የተከለከለ ነው፡፡ ይሁንና በሃይማኖታዊና ባሕላዊ ሕጎች አስገዳጅነት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሙሉ የፊት ገጽታንና ሁለቱን ጆሮዎች ያልሸፈነ መሆን አለበት፡፡ ይኸንን መመሪያ አክብሮ አለመገኘት፣

ከላይ ከተጠቀሱት ጥፋቶች አቻ/ተመሣሣይ የሆኑ ሌሎች የደንብ መተላለፍ ችግሮችን የፈፀመ ተፈታኝ ከፈተና ክፍል

/አዳራሽ ተወግዶ **ሕገ ወጥ ድርጊት ሲፈፅም የተገኘበት የፈተና ውጤት ብቻ ይሰረዛል፡፡** በሌሎች የፈተና ግዜያቶች ተገቢውን ህግ በማክበር በፈተና ላይ መቀመጥ ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የፈተና ደንብ መተላለፍ ችግሮችና ቅጣቶቻቸው እንደተጠበቁ ሆነው፡-

- በፈተና አሰጣጥ ወቅት በጣቢያው የሥነ-ሥርዓት ጉድለት አንደተፈፀመና ፈተና በሕገ-ወጥ መንገድ በግል፣ በቡድን በክፍል ደረጃ ወይም በፈተና ጣቢያ ደረጃ እንደተሰራ የሚጠቁም ማንኛውም መረጃ ከተገኘ ወይም በፈተና ውጤት መጋሸብ/መናር መነሻነት ጉዳዩ በኤጀንሲው ሲረጋገጥ በጣቢያው ያሉ ተፈታኞች ውጤት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ አንዲሰረዝና ውሣኔውን የሚመለከታቸው አካላት በጽሑፍ እንዲያውቁት ይደረጋል፣
- በማንኛውም ደረጃ በመማር ላይ ያለ አንድ ግለሰብ ለሌላ ሰው ሲፈተን ከተገኘ በሕግ አግባብ የሚጠየቅ ከመሆኑም በተጨማሪ ለአንድ ዓመት ከትምህርቱ እንዲታገድ ይደረጋል፣
- በመሆኑም ተፈታኞች ለአመታት የደከሙበትን ውጤት በነዚህ የፈተና ደንብ መተላፍ ችግሮች የተነሳ እንዳያጡ ፈተናቸውን በጥንቃቄና በተረጋጋ ሁኔታ እንዲሰሩና የሚገባቸውን ውጤት በማስመዝገብ ወደ ቀጣዩ የትምህርት እርከን እንዲሸጋገሩ የራሳቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል፡፡